«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3÷16-17



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።» መዝ. 118(119)÷130

**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org
**Copyright © 2008**



## ማውጫ

ክፍል ፩

| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት ሁለት፡- የእግዚአብሔር ቃል ........................................ | 5 |
| ፩. መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዐይነት መጽሐፍ ነው? ....................... | 5 |
| ፪. የእግዚአብሔር ቃል ባሕርያት ምንድን ናቸው? ................ | 6 |
| ፫. መጽሐፍ ቅዱስ በማን ተጻፈ? .............................................. | 7 |
| ፬. መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ? ............................................... | 8 |
| ፭. መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተጻፈ? ............................................ | 8 |
| ፮. የእግዚአብሔር ቃል በአማኝ ሕይወት ያለው ስፍራ ........... | 9 |
| ፯. መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ጥቅም ...................................... | 9 |
| ፰. መጽሐፍ ቅዱሴን እንዴት ላጥና? ...................................... | 10 |
| ትምህርት ሁለት፡- የእግዚአብሔር ቃል - ጥያቄዎች ........................ | 16 |

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው፡፡ «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን፡፡

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል፡፡ ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል፡፡ ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ፡፡

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል፡፡ አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው፡፡ ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን፡፡

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን፡፡





# ክፍል ፩




**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል፡፡»**
**መዝ. 118(119)፥130**

## ትምህርት ሁለት፡ - መጽሐፍ ቅዱስ (የእግዚአብሔር ቃል)

### ፩. መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዐይነት መጽሐፍ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ቅዱስ መጽሐፍ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ 66 መጻሕፍትን አጠቃልሎ የያዘ መጽሐፍ ሲሆን፣ ዐዲስ ኪዳንና ብሉይ ኪዳን በመባል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። ፍጥረት እንዴት እንደ ተፈጠረ፣ ሰው እንዴት በኀጢአት እንደ ወደቀና ከእግዚአብሔር እንደ ተለየ፣ ሰው ለዘላለም እንዲጠፋ እግዚአብሔር ስላልፈቀደ እንዴት የደኅንነትን መንገድ ማዘጋጀት እንደ ጀመረ ያሳያል። በተጨማሪም አዳኝ (መሲሕ) የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የሚገለጽበትን መንገድ፣ የአብርሃም ዘር በሆኑት በእስራኤላውያን በኩል እግዚአብሔር ማዘጋጀቱንና በእስራኤል መካከል እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ ይገልጻል፤ አዳኙም (መሲሑ) እንደሚመጣ በልዩ ልዩ መንገድ ደጋግሞ ያመለክታል። ዐዲስ ኪዳን ደግሞ የአዳኙን (የክርስቶስን) መምጣት በማብሠር እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያደረገውን ያስረዳል። በዐጭሩ ብሉይ ኪዳን፣ መሲሕ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ለኀጢአታችን መሥዋዕት ለመሆን እንደሚመጣ ሲያመለክት፣ ዐዲስ ኪዳን መሲሑ (አዳኙ) መጥቶላችኋል፤ የኀጢአታችሁን ዋጋ በመስቀል ላይ ከፍሎላችኋል፤ በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ አፍርሶላችኋል፤ ንስሓ ግቡ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ እያለ የምሥራቹን (ወንጌሉን) የሚያበሥር፣ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በልጁ ደም የገባው የደም ቃል ኪዳን ነው።

### የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት

**ብሉይ ኪዳን (39 መጻሕፍት)**

1. የታሪክ (HISTORICAL) መጻሕፍት (17)

   ሀ. የሙሴ የሕግ መጻሕፍት (5) (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም)
   ለ. ከኢያሱ እስከ መጽሐፈ አስቴር (12)

2. የቅኔ (POETIC ) መጻሕፍት (5)

   ሀ. መጽሐፈ ኢዮብ
   ለ. መዝሙረ ዳዊት
   ሐ. የጠቢቡ ሰሎሞን መጻሕፍት (3) (ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ)

3. የትንቢት (PROPHETIC) መጻሕፍት (17)





   ሀ. ታላላቅ ነቢያት 5 (ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል)
   ለ. ታናናሽ ነቢያት (12) (ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ)

**ዐዲስ ኪዳን (27 መጻሕፍት)**

1. የታሪክ መጻሕፍት (5)

   ሀ. አራቱ ወንጌላት ስለ ክርስቶስ (መሲሑ) ታሪክ የሚናገሩ፣ (የማቴዎስ ወንጌል፣ የማርቆስ ወንጌል፣ የሉቃስ ወንጌል፣ የዮሐንስ ወንጌል)
   ለ. የሐዋርያት ሥራ፤ የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

2. መልእክቶች (21)

ሀ. የጳውሎስ መልእክቶች (14) (ከሮሜ እስከ ዕብራውያን) (የዕብራውያን መጽሐፍ በጳውሎስ ተጽፎአል ተብሎ ቢታመንም ርግጠኛ መሆን አይቻልም)

ለ. የጴጥሮስ መልእክቶች (2) (1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ)

ሐ. የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክቶች (3)፤ (1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዮሐንስ)

መ የያዕቆብ መልእክት (1)

ሠ. የይሁዳ መልእክት (1)

3. የትንቢት መጽሐፍ፡ - የዮሐንስ ራእይ

የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መልእክት በዮሐ. 3÷16 ይጠቃለላል፤ ሰው በክርስቶስ በማመን የዘላለም ሕይወትን እንደሚያገኝና በክርስቶስ ያመነ ሰው ሊኖረው የሚገባውን ሕይወትም ይገልጻል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የተሰጠ የሕይወት መመሪያ ነው።

### ፪. የእግዚአብሔር ቃል ባሕርያት ምንድን ናቸው?

«የእውነትን ቃል እርግጥነት አስታውቅህ ዘንድ፣ ለሚጠይቅህም የእውነትን ቃል መመለስ ይቻልህ ዘንድ፤ በምክርና በዕውቀት የከበረን ነገር አልጻፍሁልህምን?» (ምሳሌ 22÷20-21)

**ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው መጽሐፍ ቅዱስ፡-**

1. የእውነት ቃል ነው። (በተጨማሪ በኤፌ. 1÷13 እና ዮሐ 8÷31-32 ይመልከቱ)
2. እርግጠኝነት ያለው ቃል ነው።
3. ለጥያቄ ሁሉ መልስ ያለው ቃል ነው።
4. በምክርና በዕውቀት የተሞላ ቃል ነው።
5. የከበረ ቃል ነው።

<u>በተጨማሪም</u>፡-

1. የማስታረቅ ቃል ነው (2ቆሮ. 5÷19)።
2. የጥበብ ቃል ነው (1ቆሮ. 2÷7)።
3. የሕይወት ቃል ነው (ሐዋ. 5÷20)።
4. ጠልቆ የሚገባና የልብን ሐሳብና ስሜት የሚመረምር ቃል ነው (ዕብ. 4÷12)።
5. የተስፋ ቃል ነው (ዕብ 10÷23)።
6. ዘላለማዊ ቃል ነው (1ጴጥ. 1÷24-25፤ ኢሳ. 40÷6-8)።
7. ጸጋን የሚሰጥ የጸጋ ቃል ነው (ሐዋ 20÷32)።
8. የእምነት ቃል ነው (ሮሜ 10÷8፤ ሮሜ 10÷17)።

<u>የእግዚአብሔር ቃል በተለያዩ ነገሮች ይመሰላል።</u>

1. ሁለት አፍ ባለው ሰይፍ (ዕብ 4÷12)፣
2. በእሳትና መዶሻ (ኤር 23÷29)፣
3. በዝናብ (ኢሳ. 55÷10-11)፣
4. በብርሃን (መዝ 118(119)÷105)፣
5. በመስታወት (ያዕ. 1÷23-25)፣
6. በምግብ (ኤር 15÷16፤ መዝ 118(119)÷103፤ 1ጴጥ. 2÷3)።

## ፫. <u>መጽሐፍ ቅዱስ በማን ተጻፈ?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የማዳን ሐሳብ የተገለጸበት መጽሐፍ ሆኖ ሳለ የጻፉት ግን አርባ የሚሆኑ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ተጠቅሞ ቃሉን በመጽሐፍ መልክ እንዳዘጋጀልን ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች ያመለክቱናል።

<u>ገላ. 1÷11-12</u> «ወንድሞች ሆይ፤ በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ አስተውቃችኋለሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም፤ አልተማርሁትምም።»

<u>2ጴጥ. 1÷21</u> «... በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።»

<u>ኤር 36÷2</u> «... የተናገርሁህን ቃል ሁሉ ጻፍበት።»





ሕዝ 1÷3 «...የእግዚአብሔር ቃል... ወደ ሕዝቅኤል መጣ።» ዮናስ 1÷1 «የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ»

ከላይ እንደ ጠቀስነው መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው አርባ በሚሆኑ ቅዱሳን ሲሆን፣ እነዚህ ቅዱሳን በተለያየ የኅብረተ ሰብና የዕውቀት ደረጃ የሚገኙ ነበሩ። ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹ፤

| | <u>ጸሐፊ</u> | <u>ሙያ</u> | <u>የጻፈው መጽሐፍ</u> |
|---|---|---|---|
| 1 | ሙሴ | እረኛ /የሕዝብ መሪ/ | ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም |
| 2 | ኢያሱ | የጦር መሪ | መጽሐፈ ኢያሱ |
| 3 | ሰሎሞን | ንጉሥ | ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ |
| 4 | ነህምያ | የንጉሥ ጠጅ አሳላፊ | መጽሐፈ ነህምያ |
| 5 | ዳንኤል | ጠቅላይ ሚኒስትር | ትንቢተ ዳንኤል |
| 6 | ማቴዎስ | ቀራጭ | የማቴዎስ ወንጌል |
| 7 | ሉቃስ | ሐኪም | የሉቃስ ወንጌል፤ የሐዋ. ሥራ |
| 8 | ጳውሎስ | ምሁር | የጳውሎስ መልእክቶች |
| 9 | ጴጥሮስ | ዓሣ አጥማጅ | የጴጥሮስ መልእክቶች |
| 10 | ዮሐንስ | ዓሣ አጥማጅ | የዮሐ. ወንጌል፣ መልእክቶችና ራእይ |

## ፬. <u>መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ?</u>

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1400 ዓ.ዓ. እስከ 400 ዓ.ዓ. ባሉት ዓመታት ውስጥ ሲሆን፣ ዐዲስ ኪዳን ደግሞ ከ45 ዓ.ም. እስከ 100 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት ውስጥ ተጻፈ።

## ፭. <u>መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተጻፈ?</u>

ሀ. ለትምህርታችን፤ «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ <u>የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና</u>።» ሮሜ 15÷4

ለ. ሊገሥጸን፤ «ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን <u>ሊገሥጸን ተጻፈ</u>።» (1ቆሮ. 10÷11)

ሐ. የዘላለም ሕይወት እንዴት እንደምናገኝ ሊያሳየን ተጻፈ፤ «<u>የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ... ጽፌላችኋለሁ</u>።» (1ዮሐ. 5÷13)

መ. በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መመላለስ እንዳለብን ሊያስተምረን ተጻፈ፤ «... <u>በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ</u>።» (1ጢሞ. 3÷15)

## ፮. <u>የእግዚአብሔር ቃል በአማኝ ሕይወት ያለው ስፍራ</u>

1. ዳግመኛ <u>የተወለድነው</u> ከእግዚአብሔር ቃል ነው (1ጴጥ. 1÷23)።
2. በመንፈሳዊ ሕይወታችን <u>የምናድገው</u> በእግዚአብሔር ቃል ነው (1ጴጥ. 2÷3)።
3. እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሆነን <u>ለክርስቶስ የምንኖረው</u> በቃሉ ነው (ዮሐ 8÷31-32)።

## ፯. <u>መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ጥቅም</u>

### 1. <u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የበለጠ ለማወቅ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የአእምሮ ዕውቀትን ለማዳበር ብቻ የሚጠና ከሆነ፣ ምንም እንኳ ሕያው ቃል በመሆኑ ለመንፈሳዊው ሕይወት የሚሠራው ሥራ ቢኖርም፣ የሚኖረው አስተዋፅኦ ግን በጣም የተወሰነ ነው። ይሁን እንጂ መጽሐፉ የሚያመለክተው ወደ ኢየሱስ፣ የሚያተኵረውም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስለ ሆነ፣ ስለ <u>ኢየሱስ ክርስቶስ ማወቁ የጥናታችን ዋናው ዐላማ ሊሆን ይገባል።</u>

«እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት ያላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው...» (ዮሐንስ 5÷39)። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን የበለጠ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ያስፈልጋል።

### 2. <u>ለመቀደስ</u>

ኢየሱስ ክርስቶስ ከጸለያቸው ጸሎቶች አንዱ ደቀ መዛሙርቱ በእግዚአብሔር እውነት እንዲቀደሱ ነው። «በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው።» (ዮሐንስ 17÷17፤ ኤፌ. 5÷26)

### 3. <u>ክፉንና በጎን ለይቶ ለማወቅ</u>

«ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው» (መዝ. 118(119)÷105)

### 4. <u>ማስተዋልን ለማግኘት</u>

«ትእዛዝህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ። ምስክርህ ትዝታዬ ነውና ካስተማሩኝ ሁሉ ይልቅ አስተዋልሁ ትእዛዝህን ፈልጌአለሁና፣ ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋልሁ።» (መዝ. 118(119)÷98-100)

### 5. <u>በጠራ መንገድ ለመራመድ</u>

«ጐልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው።» (መዝ. 118(119)÷9)

### 6. <u>እግዚአብሔርን ከመበደል ለመጠበቅ</u>





«አንተን እንዳልበድል፣ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ። (መዝ. 118(119)÷11)

### 7. <u>በሥራ መከናወንን ለማግኘት</u>

«... ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፤ አድርገውም፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ። ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው። የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቃናልሃል ይከናወንልሃልም።» (ኢያሱ. 1÷7-8)

### 8. <u>ለበጎ ሥራ ለመታጠቅ</u>

«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» (2ጢሞ. 3÷16-17)

### 9. <u>ከኀጢአት ነጻ ለመሆንና በረከትንም ለማግኘት</u>

«ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ (የእግዚአብሔር ቃል) ተመልክቶ የሚጸናበት፣ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል።» (ያዕ. 1÷25)

### 10. <u>እውነትን ለማወቅ</u>

«እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ <u>እውነትንም ታውቃላችሁ፤</u> እውነትም ዐርነት ያወጣችኋል...» (ዮሐ. 8÷31)።

### 11. እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ቃል የገባልንን <u>መንፈሳዊ ርስት</u> ለመቀበል

ሐዋ. 20÷32

### 12. <u>መንፈሳዊ ውጊያን ለመዋጋት</u>

ኤፌ. 6÷10-18

## ፰. <u>መጽሐፍ ቅዱሴን እንዴት ላጥና?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ሁሉ በየዕለቱ ሊያነበው የሚገባ የሕይወት መመሪያና መንፈሳዊ የሕይወት ምግብ ነው። ስለሆነም የጽሑፉን መልእክት ሊያስገኙ የሚችሉ የንባብና የጥናት መንገዶችን ሁሉ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ለማግኘት በሦስት አጠቃላይ መንገዶች ማለትም ዐሠሣ በማድረግ፣ በማሰላሰልና በማጥናት መጠቀም ይቻላል።

### 1. <u>ዐሠሣ</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ አንድ መጽሐፍ፣ የተጻፈበት ዐላማና የሚያስተላልፈው መልእክት ለየት ያለ የሐሳብ ክትትል አለው። ይህም ስለ ሆነ አንድን መጽሐፍ ስናጠና ቢቻል በአንድ ጊዜ ባለማቋረጥ አንብቦ መወጣት፣ ያለዚያም በተቀራረቡ ቀናት ውስጥ አንብቦ መጨረስ

<u>የመጽሐፉን ማእከላዊ ሐሳብ ለመጨበጥና ስለ መጽሐፉ አጠቃላይ ዕውቀትን ለማግኘት</u> ይረዳል። ዐሠሣ ያልነው የንባብ ዘዴ ነው፤ ለምሳሌ፦ የማቴዎስ ወንጌልን ዐሠሣዊ የአነባበብ ዘዴ ተጠቅመን በምናነብበት ጊዜ ጐላ ብሎ የሚታየው የመጽሐፉ ፍሬ ነገር የሚከተለው ይሆናል፤

- ምዕራፍ 1እና 2 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና እድገት፣
- ከምዕራፍ 3÷1 እስከ ምዕራፍ 4÷11 የአገልግሎት ዝግጅት (ጥምቀቱና ፈተናው)፣
- ከምዕራፍ 4÷12 እስከ ምዕራፍ 25÷46 የደቀ መዛሙርት መጠራትና የኢየሱስ አገልግሎት (በቃልና በሥራ በእርሱ ፈለግ በሚተኩ አገልጋዮች ወይም ምስክሮች ፊት የመጣበትን ዐላማ መግለጹ)፣
- ከምዕራፍ 26÷1 እስከ ምዕራፍ 27÷31 የኢየሱስ ዐልፎ መሰጠት (የአይሁድ ሤራ፣ የይሁዳ አሳልፎ መስጠት የኢየሱስ በሊቀ ካህናቱና በጲላጦስ ፊት መቅረብ)፣
- ከምዕራፍ 27÷32 እስከ ምዕራፍ 28÷20 የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ (የኢየሱስ መሰቀል፣ መሞት፣ መነሣትና የደቀ መዛሙርት መላክ)።

ይህ ዐይነቱ ዘዴ መጽሐፉ ስለ ምን እንደሚናገር ለማወቅና ዋና ዋና ክፍሎችን ለመጨበጥ ይጠቅማል። እንደዚሁም መጽሐፉ የተጻፈበትን ዐላማ ለመረዳት ስለሚያስችል ከቍንጽል አመለካከት ይጠብቃል።

2. <u>ማሰላሰል</u>

በየዕለቱ አንድን መጽሐፍ ወይም ብዙ ምዕራፎችን ማንበብ ከጊዜ ዕጥረት የተነሣ አይቻልም፤ ደግሞም ሁልጊዜ አስፈላጊ አይሆንም። አብዛኛውን ጊዜ አመቺ ሆኖ የሚታየው አንድን ምዕራፍ ወይም የተወሰኑ ጥቅሶችን ማንበብ ነው። ይሁን እንጂ አንባቢዎች መጽሐፉን አንብቦ ከመዝጋት ያለፈ ነገር የማያደርጉበት ጊዜ አለ። ለመንፈሳዊ ሕይወት ጠቃሚ የሚሆነው ግን <u>አንባቢው ከንባብ በኋላ ጊዜ ወስዶ ስለ አነበበው ክፍል ሲያሰላስል ነው</u>። ማሰላሰል ለጥሞና ጊዜ ከሚደረጉት ሁለት ዋና ነገሮች (ጸሎትና የቃሉ ንባብ) አንዱ ነው። ሐሳቡን ለማብራራት ያህል፣ ለምሳሌ የዕለቱ የጥሞና ጊዜ ንባብ ማቴ. 4÷1-25 ቢሆን፣ አንባቢው ይህንን ክፍል በጸሎት መንፈስ ሆኖ በሚያነብበት ጊዜ የአንባቢውን አእምሮ የሚይዙት በቍጥር 4፡7፤ እና 10 ላይ የሚገኘው «ተብሎ ተጽፎአል» የሚለው ወይም በቍጥር 19 ላይ የሚገኘው፣ «በኋላዬ ኑና ሰውን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ» ወይም «እነርሱም ... ትተው ተከተሉት» (ቍ 20 እና 22) የሚሉት ቃላትና ሐረጎች ሊሆኑ ይችላሉ። አንባቢው እነዚህን ሐሳቦች በአእምሮው ማውጣትና ማውረድ ቢጀምርና ለእኔ ምን ትርጕም አለው ብሎ ቢያስብ፣ ያነበበውን ሐሳብ እያሰላሰለ ነው ማለት እንችላለን።





3. <u>ጥናት</u>

ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱን መንገዶች ያጠቃለለ ቢሆንም <u>የበለጠ ጥልቀትና ጥራት ያለውን መረዳት ለማግኘት ዝርዝሩን (detail) በማየት የሚደረግ የማስተዋል ንባብ ነው</u>። መጽሐፍ ቅዱስ በግል፣ በአስተማሪና እንዲሁም በቡድን ውይይት ሊጠና ይችላል። ሦስቱም መንገዶች የየራሳቸው የሆነ ጥሩ የአጠናን ዘይቤ አላቸው። በዚህ ትምህርት ውስጥ የምናየው የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ነው።

## <u>የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት</u>

መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት በሩጫ የሚደረግ ነገር አይደለም። ጊዜ መወሰንን፣ ዕቅድ ማውጣትንና ለአወጡት ዕቅድ የመሰጠትን ሥነ ሥርዐት መጠበቅ (Discipline) ይጠይቃል። አንድን ጥናት አጥጋቢ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋና ዋናዎቹን እንመልከት!

1. <u>ጥሩ ዝግጅት</u>

### ሀ. <u>አእምሮንና ልብን ማዘጋጀት</u>

ጥናት ፈቃደኛነትንና ትዕግሥትን ለመማር ክፍት አእምሮንና ትሑት ልብን ይጠይቃል። ለዚህ መልካም ምሳሌዎች የቤሪያ ሰዎች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰሎንቄ ወንጌልን በሰበከበት ጊዜ ተቃውሞ ደርሶበት ነበር። በተቃውሞውም ምክንያት ከተሰሎንቄ ወደ ቤርያ ይሄድና ወንጌልን በምኵራብ ውስጥ ያስተምራል። ጳውሎስ ወንጌልን ባስተማረበት ጊዜ የቤሪያ ሰዎች ስለ አደረጉት አቀባበል መጽሐፍ ቅዱስ፣ «የቤሪያ ሰዎችም ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና ነገሩ እንዲህ ይሆንን እያሉ መጻሕፍትን በመመርመር ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉት» (ሐዋ. ሥራ 17÷11-12)ይላል። አንዳንድ ጊዜ ከሰባኪዎች የሰማነውን ወይም መጻሕፍትን ስናነብ ያገኘነውን ወይም ቀደም ሲል ያነበብነውን ደግመን ስናነብ፣ የምናውቀው ይመስለንና በቀላሉ ለማለፍ ይቃጣናል። ማለትም ክፍሉን ስናየው «ዐውቀዋለሁ» የሚል ስሜት ይመጣብንና አእምሮአችንን እንድንዘጋው ያደርገናል። መሆን ያለበት ግን የምናነበው ክፍል ቀደም ሲል የተመለከትነው ቢሆንም እንኳ፣ <u>የበለጠ</u> ለማወቅ እግዚአብሔር ዛሬም ሊያስተምረኝ ይችላል በማለት በጸሎት መንፈስ ሆኖ ክፍሉን ማጥናት ነው። አእምሮንና ልብን መክፈት ስሕተትን ለማረም፣ የቈየን ያልተስተካከለ አመለካከት ለማስተካከልና ለእውነት ብቻ ለመገዛት ጥሩ ቍልፍ ነው።

### ለ. <u>መጽሐፍ ቅዱስና መጻፊያ (እስኪሪብቶና) ወረቀት ማዘጋጀት</u>

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማእከል መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በጥናቱ ጊዜ የጥናቱ ክፍል ተከፍቶ መያዝ አለበት። በተጨማሪም ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ በጥራት ለማየት እንዲቻል የተገኘውን ፍሬ ነገርም ሆነ

ትርጕሙን ደግሞም ከሕይወት ጋር የሚዛመደውን ሐሳብ <u>በወረቀት ማስፈሩ ጥናቱን ፍሬአማ ስለሚያደርገው፣</u> ለዚህ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው።

### ሐ. <u>ከመንፈስ ቅዱስ ለመማር በጸሎት መንፈስ መሆን</u>

የሰው አእምሮ ብቻውን ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት መጨበጥ አይችልም። ስለዚህ ያስተምረን ዘንድ በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ በጣም ወሳኝ ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በቅዱሳን ሰዎች ቢሆንም በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እንደ ጻፉት ተገልጿል (1ጴጥ. 1፥20-21)። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው። … መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን <u>መንፈስ በሚያስተምረን ቃል</u> ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም» (1ቆሮ. 2፥10-16) ብሏል። በዚሁ ምዕራፍ ሐዋርያው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር በመንፈስ የሚመረመር እንደ ሆነ ይናገራል ቍ(14)። ጌታ ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት ሲናገር፣ «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤…» የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፤ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ <u>የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል</u>…» (ዮሐ. 14፥26፤ 16፥12-13) ብሎአል። እንግዲህ ቃሉ እንዲገለጥልን፣ ሐዋርያው ለኤፌሶን ሰዎች እንደ ጸለየው፣ የመንፈስ ዐይናችን እንዲበራ (ኤፌ. 1፥18) ዳዊት እንዳለውም ለሕጉ ዐይናችን እንዲከፈት (መዝ. 118(119)፥18)፣ እንደገናም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሯቸውን እንደ ከፈተላቸው (ሉቃ. 24፥45)፣ እኛም እንዲሁ ማስተዋል እንችል ዘንድ አእምሯችን እንዲከፈትልን መጸለይ ያስፈልገናል።

## 2. <u>የሚጠናውን ክፍልና የአጠናን ዘዴ መወሰን</u>

ጥናት በሚደረግበት ጊዜ እንዴት ልጀምር ምንስ ላጥና የሚል ጥያቄ ሊያጋጥም ይችላል። የሚከተሉትን መንገዶች መጠቀም ተገቢ ይሆናል፡-

### ሀ. <u>መጽሐፍ በመምረጥ</u>

ለምሳሌ፡- የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች አንድ መጽሐፍ ስለ ሆነ ይህንን መጽሐፍ መርጦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማጥናት፡-

- ጸሓፊው ማን ነው?
- የት ሆኖ ነው የጻፈው?





- መልእክቱ ለማን ነው የተጻፈው?
- መልእክቱ በተጻፈበት ጊዜ የተጻፈላቸው ሰዎች በምን ሁኔታ ላይ ነበሩ?
- የሚያስተላልፈው ዋና ሐሳብ/ሐሳቦች ምንድን ናቸው?
- ሐሳቡን ለማስተላለፍ ምን ምን መንገዶችን ተጠቀመ?
- የሚደጋገሙ ቃሎችና ሐረጎች አሉ ወይስ የሚወዳደርና የሚነጻጸር ሐሳብ ይኖርን?

በዚህ መንገድ ፍሬ ሐሳቡን ከተመለከቱ በኋላ ጸሓፊው ሊያስተላልፍ የወደደውን መልእክት ማጠቃለያ መስጠትና <u>ከራስ ሕይወት ጋር ማዛመድ</u> አንዱ መንገድ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን፣ ለግምገማ የሚረዱ ጥያቄዎችን መልስ ሁልጊዜ ማወቅ ይቻላል ማለት አይደለም። ምክንያቱም አንዳንድ መጻሕፍት በርግጥ ማን እንደ ጻፉቸው የማይታወቁ አሉ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የዕብራውያን መልእክት ነው። ይህን መልእክት ሐዋርያው ጳውሎስ ነው የጻፈው ተብሎ ቢታመንም፣ መቶ በመቶ ርግጠኛ መሆን አይቻልም።

### ለ. <u>ርእስ በመወሰን</u>

ለምሳሌ ስለ እምነት ለማጥናት ቢፈለግ፣ እምነት የሚል ቃል ወይም ስለ እምነት የሚተርክ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን አውጥቶ በጥንቃቄ በዐውደ ምንባቡ መሠረት ማጥናትና የተመረጡትን ምንባቦች በሚከተለው ንድፈ ሐሳብ ማጠቃለል ይቻላል፡-

- የእምነት ትርጕም
- የእምነት ደረጃ
- እምነት የሚገኝበት መንገድ
- የእምነት አስፈላጊነት
- የእምነት መግለጫ

### ሐ. <u>ባሕርያትን (ግለሰቦችን) በመምረጥ</u>

ለምሳሌ ስለ ንጉሡ ዳዊት ለማጥናት ቢፈለግ፣ ስለ ዳዊት የሚናገሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጥንቶ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ ይቻላል፡-

- የት ነበረ የተወለደው?

- ወላጆቹ እነማን ነበሩ?
- በየትኛው ዘመን ነበር የኖረው?
- የሚታወቅበት ነገር ምንድን ነው?
- ከእግዚአብሔር ጋር ምን ዐይነት ግንኙነት ነበረው?
- ከእርሱ ሕይወት የማገኘው ትምህርት ምንድን ነው?

### መ. <u>አንቀጽን /አንቀጾችን/ በመምረጥ</u>

ለምሳሌ፣ ማርቆስ 2፥1 እስከ ምዕራፍ 3፥6 በመጀመሪያ ምንባቡን በአንቀጽ በአንቀጽ ከፋፍሎ በማጥናት የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡-

- በያንዳንዱ አንቀጽ ምን ድርጊት እንደ ተፈጸመ፣
- አንቀጾቹ እንዴት እንደ ተያያዙ (ግንኙታቸው)፣
- አንቀጾቹ እንዴት እየጐለመሱ እንደ ሄዱ፣
- የአንቀጹ ዋና ትኵረት የትኛው ክፍል ላይ እንደ ሆነ ማየት፣
- አንቀጾቹ በዚህ መልክ በመስፈራቸው (በመደርደራቸው)፣ የጸሓፊው ዐላማ ምን እንደ ሆነ መመልከት።

### <u>ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ለአማኝ የተሰጠ ትእዛዝ</u>

ሀ. የቃሉን ወተት ተመኙ (1ጴጥ. 2፥2-3)፤

ለ. ቃሉ በሙላት ይኑርባችሁ (ቈላ. 3፥16)፤

ሐ. በቃሌ ኑሩ፤ ቃሌን ጠብቁ (ዮሐ. 14፥23፤ 15፥7)።

የዳንነውና በሕይወት የምንመላለሰው በእግዚአብሔር ጸጋ ቢሆንም፣ ለእድገትና ለተትረፈረፈ ሕይወት <u>አቋራጭ መንገድ የለውም</u>። እንዲህ ላለ ሕይወት ቃሉን እየመረመርን እንደ ቃሉ መመላለሳችን ምትክ የማይገኝለት አስፈላጊ ነገር ነው።

ጌታ በቃሉ ሙላት ይባርክዎት!





## <u>ትምህርት ሁለት፡- የእግዚአብሔር ቃል</u>

የመታወቂያ ቍጥር፤______________________________________

ስም፤ ________________________________________________

አድራሻ፤_____________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

1. መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ዐቢይ ክፍሎች ተከፍሎአል? የእነዚህ ዐቢይ ክፍሎች ዋና ዋና መልእክትስ ምንድን ነው?

2. የእግዚአብሔር ቃል በምን በምን ይመሰላል? ስለ እግዚአብሔር ቃል ባሕርይ እያንዳንዳቸው ምንን ያመለክታሉ?

3. መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሦስቱን ግለጽ።

4. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?

5. የእግዚአብሔርን ቃል በዕለታዊ ኑሮህ ተግባራዊ በሆነ መንገድ እንደ መመሪያ የተጠቀምህበትን አንድ ሁኔታ አስረዳ።

6. መጽሐፍ ቅዱስህን እንዴት ባለ መንገድ እያጠናህ እንደ ሆነ በዐጭሩ ግለጽ።

7. መጽሐፍ ቅዱስን በግል ስታጠና፣ መንፈስ ቅዱስ ሰሞኑን ከእግዚአብሔር ቃል ያስተማረህን አንድ ነገር በዐጭሩ አስፍር። (ከሰዎች የተማርኸውን ሳይሆን፣ በግል መጽሐፍ ቅዱስህን ስታጠና ሰሞኑን የእግዚአብሔር መንፈስ ያስተማረህን)